# ወታደራዊ ሞያ ቁንጅና ውድድር ኣይደለም።

ይህ ጽሁፍ ለመጻፍ ያስገደደኝ የማክብራቸ ሰው ሞቶ ኣለቃ ኣያልሰው-ደሴ የጻፉት ጽሁፍ ስለኣስገረመኝ ነው ።መቶ ኣለቃ ኣያል ሰው-ደሴ በመስከረም ወር 2016 ስለ ጀነራል ሳሞራ የጻፉትን ጽሁፍ ተሳሳቱ እንጂ ሌሎች ጽሁፋቸውን ኣድናቂ ነኝ። ለምሳሌ ከማደንቃቸው ውስጥ ጥቂቶቹን ለመጥቀስ እሞክራሎህ።”

ኣባይማ ይገደብ” የምትለው ጹሁፋቸው ጭንቅላቴ ውስጥ ቁጭ ብላለች።ሞቶ ኣለቃ ኣያል ሰው ብዙ ተቃዋሚ ነን ባዮች ዲያስፖራ ኣባይ እንዳይገደብ ብለው ያዙኝ ልቀቁኝ በሚሉበት ግዜ ነበር ኣባይ እንዲገደብ ድጋፋቸውን በጹሁፍ የገለጡ።ኣገር ወዳጅነታቸውን በግብር ኣሳዩ።መቶ ኣለቃው የኣባይ ግድብ ማንም ቢገድበው ግድቡ ለሃገራችንና ለህዝባችን ጠቃሚ ነው ብሎው በድፍረት ገልጸዋል።ኣባይ መገደቡ ለህዝባችን ይረዳል ብሎው ነው እንጂ ወያነ ሁኖው ኣይደለም።ትውልዳቸው ትግራይ ቢሆን ኖሮ ግን ‘የወያነነት’ መአርግ ይለጠፍባቸው ነበር።

ሌላ የማደንቃት የሞቶ ኣለቃ ኣያልሰው ደሴ ጽሁፍ ደግሞ እንዲህ ትላለች “የኢትዮጵያ አንድነትና የሕዝቧ ሰላም ተጠብቆ የተሻለ ሕዝባዊ-ሥርዓት እንዲኖር እንጂ የዚኽ ኋላ-ቀር አገዛዝ መወገድ በምንም መንገድ በኢትዮጵያ ኪሣራ ሊሆን እንደማይገባው ነው።ለኔ እንደገባኝ የመቶ ኣለቃው ኣባባል ስርዓቱ ብንጠላውም ኣገራችን ግን ኣናፈርስም ማለታቸው ነው።በሌላ ኣነጋገር ስርዓቱን ከምንጠላው በላይ ኣገራችንን እንውደድ ማለታቸው ነው።በሌላ ኣባባል ‘ወሃ ጠማኝ ብየ መርዝ ኣልጠጣም’ እንደሚባል የአበው ኣባባል ነው።ከሁሉ በላይ ኣገርን ማስቀደም የጥሩ ሃገር ወዳጅ መመዘኛ ነው።በዚህ መሰል ጽሁፍዎ ኣድናቂዎ ነኝ ።መቶ ኣለቃ ኣያል ሰው-ደሴ ኣከባራያቸው ነኝ።

መስከረም 2016 አትዮመድያ ስለ ጀነራልሳሞራ የጻፉት ጽሁፍ ግን ላይ ከጠቀስኩት ሃሳብ የሚጋጭ፡እንድያውም የወረደ ጽሁፍ ሁኖ ኣገኘሁት። ጀነራል ሳሞራ ገና በወጣትነቱ ኣውቀዋለሁኝ።ሞቶ ኣለቃ ኣያል ሰውም እንዲሁ ኣውቃቸውኣለሁኝ።ጀነራል ሳሞራ ማውቀው በበረሃ በትጥቅ ትግል ነው።መቶ ኣለቃ ኣያልሰው ደሴ የማውቃቸው፡መጀምርያ ካርቱም ሱዳን ነው።ኮበር ቢላ መኖርያ ቤታቸው፡ኣቶ ወርቁ ዘበኛቸው(ሁለተኛ ዘበኛቸው ረሳሁት)፡እኔና መሰሎቼ ይኖሩበት ወደ ነብሩት ቢላ መጠጋት ባንችልም እነ ዓሊ ምራሕ ሲመላለሱበት ኣውቃለሁኝ።መቶ ኣለቃ ኣያልሰው ደሴ በወጣትነት መልከ መልካም ነበሩ። ብዙ ግዜ ኣለባበስ ኣሳምረው፡ነጭ ሸሚስ ለብሰው ከነጮች ጋር ሲዘሩ ይታዩ ነበር።ጀነራል ሳሞራ በወጣትነት እድሜው እንደ መቶ ኣለቃው ኣያልሰው ደሴ ኣገራቸው ትተው መሰደድ ኣልመረጠም።ፋኖ መርቶ ጸረ-ህዝብ ደርግን መዋጋት ነበር የመረጠው።

ሁለተኛ መቶ ኣለቃ ኣያልሰው ደሴ ያገኘሁት፡የተማርነውን ኣገር የመከላከል ትምህርት ጥለን፡የገባነውን ቃልኪዳን ከድተን፡እንደ ብዙዎቹ የድሮ የመከላከያ ሃይል ተሰደን ዋሽንግቶን ላይ ኣብረን ስንፎክር ነው።አኔም የሆለታ ወታደራዊ ኣካዳሚ ሙሩቅ ነኝና። መቶ ኣለቃ ኣያልሰው ደሴ በተማሩት በኢትዮጵያ ኣየር ወለድ ኣልተማርኩም አንጂ የኢትዮጵያ ወታደራዊ ኣካዳሚ ተምሬ ኣለሁኝ።ሆለታ ወታደራዊ ትምህርት ቤት።ከጀነራል ሳሞራም በረሃ ላይ ኣብረን ወታደራዊ ትምህርት ተምረናል።በሁለቱ ቦታ የተማርኩት

ትምህርት ግን ይለያያል።ጀነራል ሳሞራ መጀመርያ ወታደራዊ ትምህርት የተማሩት ደይማ የሚባል በረሃ ነው።

መቶ ኣለቃ ኣያልሰው ደሴ 'ጀነራል ሳሞራ' ኣለባበስ ኣይችልም፡የወታደራዊ ተክለ ሰውነት እንደ ቀድሞዎቹ መኮንኖች የለውም፡ማለታቸው ኣያስገርምም።ምክንያቱ የቀድሞ መኮንኖች ተመርጠው፡በተለያየ ምርጥ ከሚባሉት ትምህርት ቤቶች ውጪ ኣገር ተልከው የተማሩ እንደ ነበሩ ናውቃለን።የተማሩትም፡ኣልጋ ማጽዳት፡ኣስተካክለህ ኣልጋ ማንጠፍ፡ጫማ ማጽዳት፡ተክለ-ሰውነት ማስተካከል ወዘተ ነው።በታሪክ ኣጋጣሚ ጀነራል ሳሞራ የመጀመርያ የወታደራዊ ትምህርት ደይማ የሚባል ትግራይ ክፍለ ሃገር ኣጋመ ኣውራጃ ነው።ከኔም ኣብረን ነው የተማርነው። ደይማ የተማርነው ወታደራዊ ትምህርትም እንደ ቀድሞ መኮንኖች ኣልጋ ማንጠፍ ልብስ ማጽዳት መልክ ማሳመር ሳይሆን የፋኖ ወታደራዊ ትምህርት ነው ።የመጀመርያ ጦርነትም ኣብረን ነው የተዋጋን።

ጀነራል ሳሞራ በወጣትነቱ በጠላት ጥይት ተደብድቦም ካዳኑት ታጋዮች ኣንዱም እኔ ነኝ። የደይማ ወታደራዊ ትምህርት ግን ከሃረር፡ከሆለታና ውጭ ኣገር ከሚማሩት ትምህርት በብዙ መንገድ ይለያል።ምክንያቱ የበረሃ ትጥቅ ትግል ትምህርት ቅንጦት ኣይደለም። ትምህርቱ ጠላትን መከላከል፡ጠላትን ማጥቃት፡ከህዝብ መጠጋት፡መመሳሰል፡የሞርልንና የእስፖርት ትምህርት፡መተኮስ፡ከመሳርያ መለማመድ ወዘተ ነው።መቶ ኣለቃ ኣያልሰው ደሴ እንደጻፉት ጀነራል ሳሞራ ኣለባበስ የማይችል ተክለሰውነት የሌለው በማለት ጽፈዋል።በኣንድ በኩል እውነትነት ኣለው።ምክንያቱ ጀነራል ሳሞራ የተማረው ወታደራዊ ሞያ እንጂ ቁንጅና ውድድር ኣይደለም።

ጀነራል ሳሞራ የተማረው ሙያ ጠላትን መክቶ፡ኣጥቅቶ ህዝብንና ሃገርን መከላከል ነው። የወታደር ሙያ ደግሞ ተዋግቶ ኣገርንና ህዝብን መከላከል ነው።መቶ ኣለቃ ኣያልሰው ደሴ የጀነራል ሳሞር የሞያ ችሎታና ኣቅም ኣላነሱም። የጀነራል ሳሞራ ተክለ ሰውነት ብቻ ነው የጻፉት። ለምን?መልሱ ግልጽ ነው።የኣንድ ወታደራዊ መኮነን እንደ ጎረምሳ መልከ መልካም ሁኖ ቆንጆ ማሳደድ ኣይደለም።ቢሆን ኖሮም ኢትዮጵያውያን ቆንጃጂት ከመልከ መልካም፡ጀግኖች ይመርጣሉ።ኣርበኞች ይወዳሉ ።

መቶ ኣለቃ የኢትጵያ ባህል የረሱት መሰለኝ። ለመሆኑ የኢትዮጵያ ኣርበኞች የት ተማሩ?ራስ ኣሉላ በኣፈር እየተኙ፡ያለ ጫማ እሾኽ እየተወጉ በጀግንነት ኣገራቸውን ተከላከሉ። ታሪክ ሰሩ።ጀነራል ሳሞራም እንደ ራስ ኣሉላ በጭቃ መሬት ላይ ተኝቶ ድንጋይ ተተርሶ እንደ ኣባቶቹ ፋሽሽት ደርግን ደመሰሰ።እነ ራስ ኣበበ ኣረጋም እንዲሁ ፋሽሽት ጣልያንን ጠራረጉ።ሁሉም ኢትዮጵያን ኣርበኞች ያሸነፉት ኣፈር ለብሰው፡ድንጋይ ተተርሰው፡ተርበው፡ተቸግረው፡ደክመው ፡ከሰል መስለው ከህዝባቸው ጎን ተሰልፈው ኣገራቸውን ተከላክለው ጠላትን ደምስሰው ኣባርረው ነጻነታቸውን ጠበቁ እንጂ እንደ መቶ ኣለቃ ኣያልሰው ደሴ ኣባባል በተክለ-ሰውነት ኣይደለም።

ወታደራዊ ሙያ ጠላትን ማሸነፍ ፡ኣገር መከላከል ነው።ጀነራል ሳሞራ ደግሞ በእሳት የተፈተነ ወታደራዊ ኣቅምንና ችሎታ እዳለው ጠላትም ወዳጂም ያውቀዋል።"ጉያ መልክዕ የብሉን ዘይምቅዳም "የትግርኛ ኣባባል ነው። የመቶ ኣለቃ ኣያልሰው ደሴ ኣባባል እውነት ከሆነ ጀነራል ሳሞራ በልብስ ኣለባበስ ከሰለጠኑት ከጦርነት ኣምልጠው ከተሰደዱት የቀድሞ

መኮንኖች በዚህ ሙያ ልምድ ስለኣላቸው የነጮች ኣገልጋይ ከመሆን ኣገራቸው ተመልሰው የጀነራል ሳሞራ ልብስ ኣልባሽ ቢቀጠሩ ኣይከፋም ባይ ነኝ።እናማ መቶ ኣለቃ ኣያልሰው ደሴ ተሳስተውል እላለሁኝ።

ከቻሉ ስህተትዎን ብያምኑ ጥሩ ነው። በብዙ ጽሁፎችዎ ብዙ ሰው እዳስተማሩ ይገባኛል። ታድያ እኔን ቅር ያሰኘኝ ስለ ጀግናው ጀነራል ሳሞራ ከወጣትነቱ ጀምሮ ህዝብና ኣገርን ለመከላከል ከባድ መስዋእትነት የከፈለ መሆኑን ጻፊው እያወቁ እኝህን ጀግና በተክለ-ሰውነቱና በኣለባበሱ መመዘኑ ያተዛዝባል።

በርሀ ሓጎስ (segud 50)

09-25-16